# ምን ብዬ ልንገረው?

ካልታወቀ ደራሲ

ገና ህፃን ሆነን አፈር ጭቃ አቡክተን፣
አንድ ላይ ተጫውተን አንድ ላይ ጨፍረን፣
ትንሽ ከፍ ስንል የኳስ ቡድን ፈጥረን፣
ሌላ ሰፈር ሄደን ሌላ ቡድን ገጥመን፣
ድል መተን ሆ ብለን የሻይ ግብዣ አድርገን፣
የእነንትና ሰፈር ብለን አስጠርተን፣
ያዬን በሥም አውቆን ሰፈርተኛው ወዶን፣
አንድ ት/ ቤት አንድ እውቀት አግኝተን፣
መውደቅን ሳናውቀው በትምህርት ጎብዘን፣
ስድስተኛን አልፈን ስምንተኛን አልፈን፣
ዘጠንኛ ገብተን ለማትሪክ አጥንተን፣
ለኮሌጅ አሰበን፣

ደግሞም መለስ ብለን የኛን ነገር ትተን፣
የሕብረተሰቡን ያገር ጉዳይ ይዘን፣
ፖለቲካ አንስተን ፖለቲካ አጥንተን፣
ጫት አንድ ላይ ቅመን ሲጋራ ተካፍለን፣
ለጭቁኖች አዝነን ሃብታሞችን ጠልተን፣
ባንድ ፍልስፍና በአንድ አመለካከት፣
ላንድ ዓላማ ቆመን፣
በትግሉ መድረክ ላይ እፊት ተሰልፈን፣
አንዱን ስንቃወም ሌላውን ደግፈን፣
ይሙት ይውደም ብለን ይኑርልን ብለን፣
ደጋፊ ፈልገን፣
የኛን ፍልስፍና ለማስፋት ፈልገን፣
ጥናት ክበብ ፈጥረን ሌላ ሰው መልምለን፣
ማታ ለውይይት ሌሎች ሰዎች ጋብዘን፣
ለሲጋራ መግዣ ለጫት ገንዘብ አጥሮን፣
ሰዓት ልብሳችንን ሃራጅ ብለን ሸጠን፣
ድሮም የኛ አይደለም የሕዝብ ነው ብለን።
ሥርዓት ልንቀይር ከኛ ልንጀምር፣
የእኔ እሚባል ትተን፣
ሁሉንም አክብረን፣
ሴት መልከፍ አቁመን፣

እህት ጓዲት ብለን፣
በረንዳ ቁጭ ብለን ከኩሊ ጋር አውርተን፣
ንቁ ተደራጁ ተባበሩ ብለን፣
ድሉ የሕዝብ ነው እናሸንፋለን፣
የኛን እንጉርጉሮ መዝሙራችን አርገን።
የኢትዮጵያ ጭቁኖች ከዓለም ጭቁን ጋራ
ዘመድ ናቸው ብለን፣
ከዓለም ፈላስፋዎች ብዙ ትምህርት ወስደን፣
የብዙ ሀገር ትግል ተመክሮ አጥንተን፣
ቀይ ባንዲራ አንስተን መፈክር አንግበን፣
ሕዝብ ለመቀስቀስ ሰልፍ ቦታ ይዘን ፣
አብረን ተሰልፈን መዝሙር አሰምተን፣
ወታደር መጥቶ ብን ጥይት ተኩሶብን፣
በጥይት በትኖን፣
ከዛ ቀን ጀምሮ ሳንገናኝ ኖረን፣
አስር ዓመት አልፎ አስራ ሁለት ሆኖን፥
ያንን አብሮ አደጌን ያንን ጓደኛዬን፣
ብቻዬን ብቻውን አንድ ቀን ባገኘው፣
ሳስበው ጨነቀኝ፣
ምን እንደሚነግረኝ ምን እንደምነግረው።

ያንን ጓደኛዬን ያንን አብሮ አደጌን፣
ገና ሳላገኘው፣
ነገሩ አሳሰበኝ በሃሳቤ አውጥቼው፣
የት እንደ ነበረ ቀድሜ ጠይቄው፣
ማን ምን እንደሆነ የት እንደደረሱ፣
ያየውን ለማወቅ ቅድሚያ እድል ሰጥቼው፣
ያን ግዜ ሰልፍ ላይ ጥይት እኔን መቶኝ፣
ወድቄ ተኝቼ ወታደር አግኝቶኝ፣
እስር ቤት ወስደውኝ ከርቸሌ ልከውኝ፣
አስር ዓመት ሙሉ ማንም ሰው ሳያየኝ፣
ፍርድ ቤት ሳልቀርብ ሳይፈረድብኝ፣
ይግባኝ ሳላሰማ ምስክር ሳላገኝ፣
ባለፈው ዓመት ነው በምህረት የፈቱኝ።
ለምን እንደፈቱኝ፣
ስህተትም ነው ብለው እንሹራንስ አልሰጡኝ።
ብሎ በማፌዜ ሳቅ ፈገግ ብሎ አሳቀኝ።

ፀጉር መመለጡን መንጣት መገርጣቱን፣
ጎንበስ ብሎ አሳየኝ፣
እንዳጎነበሰ ያለፈው ትዝ አለው፣
ዐይኑ ደም ለበሰ ሰውነቱን ሞቀው።
እነንትና ደግሞ ላመኑበት ቆመው፣
ባመኑበት ጸንተው፣
ስልጣን ሳይጠማቸው
ስልጣን ሳይሸታቸው፣
ወይ ሳይሸሹ ፈርተው፣
ታግለው ሊያታግሉ ምንም ሳይታከቱ፣
እትግሉ መድረክ ላይ የጀግና ሞት ሞተው፣
እነንትና ደግሞ እጃቸውን ሰጥተው፣
ጠቁመው ሰው አሲዘው፣
ስልጣን ተቀብለው ስልጣን ተሸልመው፣
እዛው አራት ኪሎ ትልቅ ቦታ አላቸው።
እነንትና ደግሞ ይኸኛው ሲፈርስ ለዛኛው
ገብረው፣
ለጊዜውም ቢሆን ስልጣን ተቀብለው፣
በኋላ ተይዘው አራት ኪሎ ሄደው፣
ባርጩሜ ተገርፈው
አሁን ትፈታላችሁ የሚል ወሬሰምተው፣
መስከረም ሁለትን እየጠበቁ ነው።
እነንትና ደግሞ ያንኪ ጎ ሆም ያሉት፣
ያንኪ አገሩ ሄደው፣
ያሳደዱ መስለው ተሰደው የቀሩት፣
እውጭ መሆናቸው አልፎ አልፎ ቢወራም፣
ምን እንደሚሰሩ ምን እንደሚያስቡ የሰማነው
የለም።
በኔ በኩል ያለው ባጭሩ ይሄ ነው፣
እስቲ አንተ ንገረኝ
ምን አስባችኋል ? ተስፋው በእናንተ ነው።
ብሎ ቢጠይቀኝ
ያንን ጌደኛዬን ምን እንደምነግረው፣
ሳስበው ጨነቀኝ
የማንደብቀው ነውና የምንተማመነው፣
ልነግረው ያሰብኩት ባጭሩ ይኸ ነው።
እንትናና እንትና ሱዳን ተገናኝተው፣
ትግሉ ከፈረሰ እንጋባ ብለው፡
እሷ ፈርማለት እሱም ፈርሞላት፣
ግሪን ካርድ የሚባል ወረቀት አውጥተው፡
እዛው አሜሪካ ፈረንጅ አገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ያንኪ ጎ ሆም ያሉት
ያንኪ አገሩ ሲሄድ ያንኪን ተከትለው፣
ያንኪ ሃገር የሄዱት
ዛሬ ከያንኪ ጋር ለመኖር ተስማምተው፣
እዛው አሜሪካ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ታክሲ ነጂ ሆነው፡
እነንትና ደግሞ የመኪና እረኛ ጠባቂዎች ሆነው፡
ገንዘብ አጠራቅመው፣
ሱቅና ምግብ ቤት ጋዝ ስቴሽን ከፍተው፡
እዛው አሜሪካ ፈረንጅ አገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ፍልስፍና ትተው፡
ቁጥርና ሳይንስ የሞተር አሰራር፣
የህንጻ ግንባታ ኤሌትሪክ አጥንተው፣
በየመስሪያቤቱ መሃንዲስ ተብለው፣
ፖለቲካ ነገር ሰው ሲያነሳባቸው፣
እንዳልነበሩበት እንዳልሰሙ ሰምተው፣
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ አገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ዛሬም እንደድሮው፣
ቆሸሽ ያለ ለብሰው፣
ፖለቲካ ነገር ሁልጊዜም ቢያወሩም፣
ቃላት አልለወጡም ሃሳብ አልጨመሩም።
ስላለፈው ውድቀት እውነቱን አውጥተው፣
ታሪኩን አልጻፉም፣
ለወደፊቱም ታሪክ ሰሪ አይደሉም፥
ሰዓቱ እየሄደ እድሜአቸው ቢገፉም፣
ጊዜ ወርቅ አይደለም እነሱ አይቆጥሩትም።
ለወሬ የሚመች ሰፊ ሀገር ነውብለው፣
እዛው ባሕር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ባለፈው ድርጅት በትግሉ
ተናደው፣
ድሮም መዓበሉ ነበር የያዛቸው፣
ዛሬ ፖለቲካን እክ እንትፍ ብለው፣
ሌላ ስልጣኔ ጆሊነት ጀምረው፣
ቆዳ ሱሪ ለብሰው፣
በሬጌ ሙዚቃ በግራዋ ሰክረው፣
እዛው ባሕር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነትና ደግሞ ጧት ጧት ይሰራሉ፣
ማታ ይጠጣሉ።
ወይ እንደነእንታና ገንዘብ አጠራቅመው፣
በሀብት አልከበሩ ፣
ወይ እንደነንትና ት/ቤት ገብተው፣
ትምህርት አልተማሩ፣
ወይ እንደነእንትና ጆሊነት ጀምረው፣
ሬጌ አልዘፈኑ፣
በመጠጥ ብዛት ተጠብሶ ፊታቸው፣
አምቢ ተቀብተው መስሎ የላጣቸው፣
ቶሎ እየተቆጡ ሰው ሲያናግራቸው፣

እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ፖለቲካ ሳይንስ ኢኮኖሚ
አጥንተው፣
ትልቅ ቦታ ይዘው ፕሮፌሰር ተብለው፣
በየስብሰባው ላይ ተጠሪዎች ሆነው፣
ተወካዮች ሆነው፣
ለኢትዮጵያ ጠቃሚው IBM ቢገባ ንግድ
ቢስፋፋ ነው፣
የሚል ሃሳብ ይዘው፣
ዛሬም እንደ ድሮው ፣
ከሶቬት ጠብቀው ቻይናን ተመልክተው፣
ጋርቫቾቭ ጥሩ ነው የቻይናው የኛ ነው፣
ማለት ቢጀምሩም፣
እንዴት እንደሚሆን መንገድ አላሳዩም።
ለወሬ የሚመች ሰፊ ሀገር ነው ብለው፣
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ዛሬም እንደድሮው፣
ለእውነት ለመስራት መፍትሄ ለማግኘት ከልብ
ቢጥሩም፣
ሰውን ማደራጀት መቀስቀስ ከብዷቸው፣
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ዛሬም ት/ቤት ከኮሌጅ
ቢሆኑም፣
መማር ማስከበሩ ምሳሌ ቢሆንም፣
ለመቼ እንደሆነ በደንብ አልገባንም።
ሥራ ባይጀምሩም አንድ ቀን ጨርሰው፣
ጡረታው ከፍ ይላል የሚል ወሬ ሰምተው፣
እዛው ት/ ቤት ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ እኩልነት ትተው፣
በወንድ ለመከበር ለመኖር ወስነው፣
ቀለም ተቀብተው በጌጣ ጌጥ ደምቀው፣
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ ሦስሙቶ ስልሳ ቀን ሥራ
ይሰራሉ፣
ጳጉሜ ጳጉሜ ሲደርስ እየተገናኙ ኳስ
ይጫወታሉ።
የኢትዮጵያ ቡድን ድሮ የምናውቃቸው፣
እዛው አሜሪካ ፈረንጅ አገር ናቸው።

እነንትና ደግሞ ለሥራ ተልከው፣
ሥልጣን በቃን ብለው አሳይለም ጠይቀው፣
እጃቸውን ታጥበው ንጹህ ሰዎች ሆነው፣
መጽሐፍ ደርሰው በቲቪ ተናግረው፣
ለቃለ መጠይቅ በሬዲዮ ቀርበው
ታሪክ አዋቂዎች ምስክሮች ሆነው፣
ዛሬም እንደድሮው ነግደው አትርፈው፣
እነሱ ተናግረው እኛን ሰሚ አድርገው፣
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ አገር ናቸው።
እነንትና ደግሞ እነንትና ደግሞ እነንትና ደግሞ፣
ብዬ ያየሁትን እውነቱን ልነግረው
ወይስ እንዳያዝን ይበልጥ እንዳይከፋው፣
እውነቱን ሸሽጌ በውሸት ሸፍኜው፣
እንዴው በደፈናው ሁሉም ደህና ናቸው።
ያለፈውን ውድቀት ስህተቱን ተረድተው፣
ለማረም ወስነው፣
ባንድ ድርጅት ሥር ባንድ አመለካከት፣
ላንድ ዓላማ ቆመው፣
የተሻለ ነገር ሊወስዱ ሀገራቸው፣
እየተዘጋጁ እያሰቡበት ነው።
ብዬ ላስደስተው?
ያንን አብሮ አደጌን ያንን ጓደኛዬን፣
ቀን የለያየንን፣
ደግሞ ቀን ወቶልን፣
ቀን ለኛ ሆኖልን፣
አንድ ቀን ባገኘው፣
ሳስበው ጨነቀኝ፣
እስኪ መላ ስጡኝ።
ምን ብዬ ልንገረው ?